# የልዕልት ሶፍያ ደስታ

## አጭር የሕይወት ታሪክ

# *Her Imperial Highness*
# *Princess Sophia Desta*

## Short Biography



## ጥር 17, 1926 - ኅዳር 2, 2014

### January 25, 1934 – November 11, 2021

በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤
መጽሐፈ ምሳሌ - ምዕራፍ 3 ቁጥር 5

Trust in the Lord with all your heart and lean not on your own understanding.

Proverbs Chapter 3 Verse 5

# ልዕልት ሶፍያ ደስታ



ልዕልት ሶፍያ ደስታ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እና የግርማዊት እቴጌ መነን ልጅ ከሆኑት ከልዕልት ተናኘ ወርቅና ከጀግናው የጦር መሪ ከራስ ደስታ ዳምጠው በጥር 17 ቀን 1926 ዓ.ም በከፋ ጠቅላይ ግዛት ጅማ ከተማ ተወለዱ።

ፋሽስት ኢጣልያ ከ1928 ዓ.ም እስከ 1933 ዓ.ም ኢትዮጵያን በወረረበት ዘመን ጀግናው ራስ ደስታ ዳምጣው በአገሪቷ ደቡብ ክፍል የሚገኘውን ሰራዊት በመምራት ጠላት ኢጣልያንን ሲመክቱ ቆይተው በጦር ሜዳ ተማርከው በ1929 ዓ.ም ተሰውተዋል።

ልዕልት (በወቅቱ እመቤት ሆይ) ሶፍያ ገና በሕፃን እድሜያቸው ከእናታቸው እና ከንጉሣውያን ቤተሰብ ጋር ስደት ሲሄዱ ከአብሮ አደጋቸው ልዕልት እጅጋየሁ አስፋወሰን ጋር መጀመሪያ በኢየሩሳለም በኋላም በእስክንድርያ ግብፅ አገር ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። ከ አንድ ዓምት በኋላ ቤተሰቦቻቸው ወዳሉበት እንግሊዝ አገር በመሄድና ከእህቶቻቸው ጋር በመቀላቀል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በክላርንደን ት/ቤት ተከታትለው አጠናቀዋል። እንዲሁም ከፍተኛ ትምህርታቸውን በሮሃምፕተን ዩኒቨርሲቲ ፍሮቤል ኢንስቲትዩት ተከታትለው በአስተማሪነት የባችለር ዲግሪ ተመርቀዋል።

እመቤት ሆይ ሶፍያ ወደ ሃገራቸው ከተመለሱ በኋላ የጀግናው አርበኛ የኃይለማርያም ምሞ ልጅ ከሆኑት ከሻምበል ደረጀ ኃይለማርያም ጋር በኢትዮጵያ ወግና ባህል መሠረት በጥር 1951 ትዳር መስርተው ከአያታቸው ክግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴ የልዕልትነት ማዕረግ ተቀብለዋል።

በታህሳስ 1953 ዓ.ም የክብር ዘበኛ መሪዎች ባካሄዱት የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ላይ የንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ ኃይሎች አንዱ የነበሩት ሻምበል ደረጀ ኃይለማርያም በግዳጁ ላይ በመሰዋታቸው ባለቤታቸው ልዕልት ሶፍያ ደስታ ጥልቅ ሀዘን ደርሶባቸዋል። አምላክ ግን ስም መጠሪያ እንድትሆናቸው ሐናን(መታሰቢያ) በመውለዳቸው የካፒትን ደረጀን ሕልፈት በመቻልና በምስጋና አሳልፈውታል።

ቢሆንም ምሕረቱ የማያልቅበት አምላክ ስሙ እንዲከብር እና እንዲሰፋ በነበራቸው ምኞት መሰረት “እንጦጦ ኢንተርናሽናል ት/ቤት” በሚል ስም የግል ት/ቤት አቋቋሙ። ትምህርት ቤቱ ለአቅመ ደካማ ልጆች የትምህርት ዕድል በመስጠት ተማሪዎቹ ጥራት ያለው ትምህርት የሚያገኙበት እድል ከፍተውላቸው ነበር።

ልዕልት በተጨማሪም ንጉሣዊ ቤተሰብ በሚያካሂዱት የበጎ አድራጎት ሥራዎች የተሳተፉ ሲሆን በተለይ ቼሽር ኢትዮጵያ የተባለው የአካል ጉዳተኞች ት/ቤትና የኢትዮጵያ ወጣት ሴቶችን ክርስትያን ማህበር (ወሴክማ) ድርጅትን በማቋቋም ላይ ታላቅ አስተዋፅኦ ያደረጉ ሲሆን፤ ለሰው ተቆርቋሪነታቸውን፥ ሁሉን ሰው በእኩል ዓይን ማየታቸው፥ ደግነታቸው፥ ምንም ጊዜም የሚመሠከርላቸውና ሲታወሱ የሚኖሩ ባሕሪዎቻቸው ናቸው።

እንደ እህቶቻቸውና መላው ንጉሣዊ ቤተሰብ ልዕልት ሶፍያም አያታቸውን ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴን በጣም ይውዳቻው ስለነበር ከቤተመንግስት አይለዩም ነበር። እንዲሁም ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ውጭ ሀገር ጉብኝት በሚያደርጉበት ጊዜ አብሮ በመሄድ ዩጎዝላቪያ፣ ማሌዥያ፣ ካምቦዲያ፣ ታይላንድ፣ አውስትራሊያ፣ ጃማይካና ትሪናዳድ ቶቤጎን ጎብኝተዋል። እነዚህም ጉቢኝቶች የአለም መግናኛ ብዙሃን በውቅቱ በሰፍይው ይዘግቡት ነበር።

በመስከረም 1967 ዓ.ም በተፈፀመው መፈንቅለ መንግሥት አምባገነኑ ደርግ ስልጣን ሲይዝ ከእናታቸው ከልዕልት ተናኘ ወርቅ ከእህቶቻቸው ልዕልት አይዳ፣ ልዕልት ሰብለ፥ ልዕልት ሒሩት እና ከሌሎች ንጉሣዊ ቤተሰብ አባላት ጋር "ዓለም በቃኝ" ተብሎ በሚታወቀው እስር ቤት በጽኑ እስራት ለ14 ዓመታት ተንገላተዋል። በዚህ ከባድ ዘመን ታናሽ ወንድማቸው ሪር አድሚራል እስክንድር ደስታ ከ60ቹ የንጉሣዊው መንግሥት ሚንስትሮች እና ባለስልጣኖች ጋር ተገድለውባቸዋል። ከዛም ከአንድ ዓመት በኋላ አያታቸው ግርማዊ አፄ ኃይለ ሥላሴም በግፍ ተገድለዋል። በዚህ የችግር እና ሐዘን ግዜ ግን ልዕልት ሶፊያ ሳይበገሩ እስር ቤት ውስጥ ለተወለዱ ሕጻናት ትምህርት ቤት አቋቁመው ያስተምሩ ነበር።

በኃያሉ እግዚአብሔር ፈቃድ በ1981 ዓ.ም ልዕልት እና ሴት ቤተሰቦቻቸው ከእስር ከተፈቱ በኋላ ከእናታቸው ልዕልት ተናኘወርቅ እና ከልዕልት እህቶቻቸው ጋር በመሆን ለአረጋዊ እናት የሚገባውን ፍቅርና እንክብካቤ አድርገዋል። ከዚህም በላይ የልጅ ልጃቸውን ልጅ ደስታ አስፋውን ተመላልሰው በመጎብኘት የአያትነት ፍቅራቸውንና የዕድገቱን ክትትል በፍቅርት ፈጽመዋል። ከእስር ከተፈቱ በኋላ ልዕልት ሶፊያ ከልጃቸው ከእመቤት ሀና ማርያም ጋር በጣሊያን አገር የማይረሳ ቆይታ አድርገዋል። ልዕልት ሶፊያ ለብዙ አመታት ልጃቸውን እና የልጅ ልጃቸውን አሜሪካ በሚገኘው ቤታቸው በመምጣት እና በመጠየቅ ብዙ አስደሳች ጊዜ አሳልፈዋል። እንደዚሁም እናታቸው ልዕልት ተናኘወርቅ ፣ እህቶቻቸው ልዕልት አይዳ፣ እና ልዕልት ሰብለ፥ የእህታቸው የልዕልት አይዳ ልጅ የሆኑት ልጅ ሚካኤል በሚኖሩበት በአሌክሳንድሪያ፣ ቨርጂኒያ በተደጋጋሚ እየሄዱ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ጥሩ ጊዜ አሳልፈዋል።

ልዕልት በጄኔቫ ስዊዘርላንድ ለተውሰነ ጊዜ ኖረዋል። ጄኔቫን ለረዥም ጊዜ የሚያውቁት አገር በመሆኑ እና ብዙ ውዳጆች ያፈሩበት ቦታ በመሆኑ ተመችቷቸው ኖረዋል። እናታቸውን እና እህቶቻቸውን በጄኔቫ ሐይቅ ዳርቻ እየጋበዙ የማይረሱ የእረፍት ጊዜ

ያዘጋጁላቸው ነበር። እነዚህ የውጪ እረፍት ጊዜያት በእድሜ ለገፉት እናታቸው ልዕልት ተናኘወርቅ የፈውስ እና የእረፍት ጊዜ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። እናታቸው በታመሙ ጊዜ ልዕልት ሶፊያ ከጎናቸው አልተለዩም።

በኋላም በጣም ከሚቀርቧቸው እህታቸው ልዕልት ሒሩት ደስታ ጋር ለመኖር ወደ ለንደን ሄዱ። ለንደን በሚኖሩበት ግዜም ብዙ ጊዜ አክስታቸውን ልዕልት ዙሪያሽወርቅ ገብረእግዚአብሔርን ይጠይቁ ነበር። ልዕልት ዙሪያሽወርቅ እና ልዕልት ሶፊያ ጥልቅ የሆነ የእህትማማች ትስስር ስለነበራቸው የልዕልት ዙሪያሽወርቅ ከዚህ ዓለም በሞት መለየት ልዕልት ሶፊያን በጣም ጎድቷቸው ነበር። ልዕልት ሶፍያ በለንደን የሚገኘው የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ በሰፊው ታዋቂ ሰው ነበሩ። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ በህዝብ ማመላለሻ ስለሚመላለሱ እና መንገድ ላይ የሚያገኙትን ኢትዮጵያዊ በሙሉ ሰላምታ ሰትተው ስለሚተዋወቁ ነበር። ለማንኛውም ሰው የነበራቸው ክብር እና ፍቅር፥ ከሁሉም በላይ ታላቅ ትህትናቸው "የህዝብ ልዕልት" የሚል ቅጽል አስገኝቶላቸዋል።

ለሀገራቸው ትልቅ ፍቅር የነበራቸው ልዕልት ሶፊያ ደስታ ወደ ኢትዮጵያ ለአያታቸው ለአፄ ኃይለ ሥላሴ እና ለእናታቸው ለልዕልት ተናኘወርቅ ቀብሮች፥ እንዲሁም ወዳጅ ዘመዶቻቸውን ለማየት ተመላልሰዋል።

ልዕልት ሶፍያ ባደረባቸው አጭር ህመም ሕዳር 11 ቀን 2014 በለንደን ከተማ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ከሚወድዋቸው እህታቸው ልዕልት ሰብለ ደስታ፣ ልጃቸው እመቤት ሐና ማርያም ምህረተ ሥላሴ ደረጄ፣ የልጅ ልጃቸው ልጅ ደስታ አስፋው፣ እንዲሁም ብዙ የእህቶቻቸው ልጆች እና የቤተሰብ አባላት ሲለዩ ትልቅ ሐዘን ጥለዋል። በተለይ የልዕልት ሶፍያ ለእህቶቻቸው ልጆች ሚካኤል፣ ዮሐንስ እና ስዩም መንገሻ፥ እመቤት ጆቴ የሺ እና ላሊ ካሳ በልባቸው ውስጥ ልዩ ቦታ ነበራቸው። ከወጣትነቷ ጀምሮ የሚያውቋቸው አማቻቸው ከልዕልት ማሕጸንተ ሀብተ ማርያም ጋር ጥሩ ወዳጅነት እና ልዩ ቅርበት ነበራቸው። ልዕልት ሶፍያ ለቤተሰባቸው ታላቅ ፍቅር የነበራቸው፣ ከራስ ወዳድነት ነፃ የሆኑ፣ የመንፈስ ልግስና፣ በትጋት እና ያለመታከት ለበጎ አድራጎት ስራ የነበራቸው አስተዋጾ ሊካድ አይችልም። ለኢትዮጵያውያን ልጆች ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ህጻናት እና ለሰው ልጆች ትምህርት እና ደህንነት ያላቸው ቆራጥ አቅዋም አይዘነጋም።

እህታቸው ልዕልት ሰብለ ደስታ፥ ወይዘሪት መተአስቢያ መሳይ፣ ልጃቸው እመቤት ሀና ማርያም፣ የልጅ ልጃቸው፣ ልጅ ደስታ አስፋዋ እና የእህቶቻቸው እና የወንድማቸው ልጆች

እንዲሁም ሰፊው ቤተሰቦቻቸው እና ወዳጆቻቸው በሙሉ ሁሌም በፍቅር እያስታወሷቸው ይኖራሉ። መላው ቤተሰብ ልዕልት ካለፉበት ግዜ ጀምሮ ከቅርብም ከሩቅም ስለሃዘናቸው ምልእክትየላኩላቸውን ሁሉ የከበረ ምስጋናቸውን መግለጽ ይፈልጋሉ።

ልዕልት ሰብለ ደስታ፥ ወይዘሪት መተአስቢያ መሳይ፣ እመቤት ሀና ማርያም፣ ልጅ ደስታ
አስፋዋ እና መላው ንጉሣዊ ቤተሰብ።

ኃያሉ እግዚአብሔር የልዕልት ሶፊያን ነፍስ በአጸደ ገነት ያኑርልን። ነፍሳቸውን
ይማር። ለመላው ቤተሰብ ጽናቱን ይስጥልን።

# *Her Imperial Highness*
# *Princess Sophia Desta*



Princess Sophia Desta was born in the city of Jimma, in the Keffa Province of Ethiopia, on January 25, 1934 to Ethiopia's great war hero Ras Desta Damtew, and Her Imperial Highness Princess Tenagnework Haile Selassie. Princess Sophia was thus a granddaughter of Emperor Haile Selassie I and Empress Menen Asfaw. When Ethiopia was occupied by the forces of Fascist Italy in 1935, her father Ras Desta led Ethiopian forces on the Southern front. He was captured and summarily executed by the fascists in February 1937. Her mother Princess Tenagnework was forced to go into exile with her children and the rest of the Imperial family to avoid capture by the fascist forces. The family first went to Jerusalem where Princess Sophia and her cousin Princess Ejegaeyhu Asfawossen spent their happy childhood. These early years is where their great friendship started and later continued for a long time when both of them returned to Ethiopia after the end of the second world war before Princess Ejegaeyhu tragically passed away in prison in 1976.

Princess Sophia later attended school in Alexandria, Egypt and afterwards joined her sisters to continue her education at Clarendon School in the United Kingdom. Her time as a student at Clarendon was marked by the long term and special friendships she fostered with her classmates and colleagues. This was evident especially in the remaining years of her life in London where her Clarendonian friends visited her and keep in close contact. She pursued her higher education at Froebel Institute at the University of Roehampton where she graduated with a B.A. in Education, majoring in teaching. She was married in January 1959 in Addis Abeba to

Captain Dereje Haile Mariam, son of war hero Lij Haile Mariam Mamo when her grandfather, Emperor Haile Selassie accorded her with the rank of Princess. A year later, she was widowed when Captain Dereje was killed fighting as he defended the Emperor in the attempted Imperial Guard coup d'état of December 1960. In addition to raising her daughter, Emebet Hannah Mariam Princess Sophia's house was home to many children of extended family members who she had adopted as her own.

Princess Sophia established a private institution, the Entoto International School, which she ran personally. The school offered high academic studies to the international community and scholarships for Ethiopian students who came from underprivileged backgrounds, thus giving them opportunities to benefit from a higher quality education. She was also involved in the many philanthropic efforts of the Imperial family including establishing Cheshire Homes Ethiopia, which was first started in her home, and working with the YWCA (Young Women's Christian Association), which provided support and training for young Ethiopian women and helped to enhance their livelihood.

Like her siblings and other family members, Princess Sophia Desta enjoyed a very close relationship with her grandfather, His Imperial Majesty Emperor Haile Selassie, and was a frequent visitor at the Jubilee Palace. One of her daily duties was to recap the nightly news from the BBC and other international news channels. She accompanied His Imperial Majesty on several of his foreign State visits, most notably to Yugoslavia, Greece, Malawi, Malaysia, Cambodia, Thailand, Australia, Jamaica, and Trinidad and Tobago.

Princess Sophia was among the members of the Imperial family that were imprisoned by the Marxist Derg regime upon the overthrow of the Ethiopian Monarchy in September of 1974. She and her close family endured a harsh imprisonment in the notorious prison known as *Alem Bekagne* or "End of the World" for 14 years. During this time Princess Sophia lost her younger brother, Rear Admiral Iskindir Desta who was killed alongside 60 prominent members of the Emperor's government and a year later her grandfather who was murdered by the Marxist Derg regime. Never one to be defeated she set up a makeshift school for children born

in prison. She, her sisters, mother and other close family members were finally freed in 1988.

After her release Princess Sophia and her daughter Emebet Hannah Mariam had a memorable reunion in Rome, Italy and throughout many years Princess Sophia spent many joyful times visiting her daughter and her grandson Lij Desta Asfaw at their home in the United States. She also was frequently in Alexandria, Virginia where her mother Princess Tenagework, her sisters Princess Aida and Princess Seble, and her nephew Lij Michael Mengesha lived.

Later the Princess settled in Geneva, Switzerland, a city she knew well and where she had many friends and associates. She often organized memorable holidays which included visits of her mother Princess Tenagnework and her sisters to this lake side city. Princess Sophia also made sure that these vacations abroad were a healing and restful time for her then aging mother, Princess Tenagnework. When her mother became ill, Princess Sophia never left her side.

She then moved to London to live with her sister Princess Ruth Desta, with whom she was very close. She was also a frequent visitor at her cousin Princess Zuriashwork's home. Princess Zuriashwork and Princess Sophia shared a deep bond and the death of Princess Zuriashwork was a big blow to Princess Sophia who treasured her company and sisterly love. In addition, Princess Sophia was a well-known figure in London's Ethiopian community because she would often be seen using public transport and greeting every Ethiopian she might meet in the street. Her big heart for others and her great humility lead her to be called the "People's Princess". A great admirer and lover of her country, she returned to Ethiopia, her beloved homeland, and place of birth to visit her relatives, then for the solemn funeral of His Majesty Emperor Haile Selassie, and later that of her mother, Princess Tenagework.

Princess Sophia had a special place in her heart for all of her family and in particular for her nephews Lij Michael, Yohannes, and Seyoum Mengesha and as well as her nieces Emebet Jote and Yeshi and Laly Kassa.

She also enjoyed a great rapport and affinity with Princess Mahezent Habte-Mariam, her sister-in-law who she has known since her youth. Princess Sophia will be best remembered for her great love of family, selflessness, and generosity of spirit. Her dedication and tireless charity work, as seen through her avid commitment to the education and welfare of not just Ethiopian children, but all children and humanity alike, will remain her long lasting legacy.

After a brief illness Princess Sophia passed away in London on November 11, 2021. She is survived by her sister Her Highness Princess Seble Desta, her daughter Emebet Hannah Mariam Meherete Selassie Dereje, her grandson Lij Desta Asfaw, as well as many nephews and nieces and family members.

She will be dearly missed by her sister Princess Seble Desta and Woizert Metasebia Messai, her daughter Emebet Hannah Mariam, her grandson, Lij Desta Asfaw and her many nephews and nieces and all her family and friends by whom she has long been held in great affection.

All of the family would like to express their deep-felt thanks and gratitude to all those near and far who have expressed their sorrow and support at the passing of the Princess.

May God rest the soul of Princess Sophia Desta among the blessed, and may her memory be eternal.



*Princess Sophia with her mother, Princess Tenegnework, sisters, Princess Aida & Princess Ruth, & her daughter Emebet Hannah Mariam*
*ልዕልት ሶፊያ ከእናታቸው ከልዕልት ተናኘወርቅ እና እህቶቻቸው ልዕልት አይዳ እና ልዕልት ሒሩት፥ እና ልጃቸው እመቤት ሀና ማርያም*



*Left to Right: Emebet Hannah Mariam, Princess Sophia Desta & Woizero Gizework Wolde-Selassie*
*እመቤት ሀና ማርያም እና ልዕልት ሶፊያ ደስታ ከወ/ሮ ጊዜወርቅ ወልደ ሥላሴ*



*Emebet Hannah Mariam and Princess Sophia Desta on Princess Sophia’s 86th Birthday*
*እመቤት ሀና ማርያም እና ልዕልት ሶፊያ በ86ኛው ልደታቸው።*



*Emebet Jote Kassa, Princess Sophia, & Emebet Yeshi Kassa*
*እመቤት ጆቴ. ካሳ ልዕልት ሶፊያ ደስታ እና እመቤት የሺ ካሳ።*



*Princess Sophia visiting Princess Aida & Luel Ras Mengesha and family*
ልዕልት ሶፊያ የልእልት አይዳ እና የልዑል ራስ መንገሻን ቤተሰብ ሲጠይቁ።



*Princess Sophia with Lij Seyoume Mengesha, Emebet Zenamariam & Emebet Isabella Mengesha*
*ልዕልት ሶፊያ ከልጅ ሰዩም መንገሻ እና እመቤት ዜናማርያም እና እመቤት እዝአቤላ መንገሻ።*



*Princess Sophia with His Majesty & the Imperial Ethiopian family hosting the Royal House of the Netherlands (c. 1970s)*
*ልዕልት ሶፊያ ከግርማዊ ጃንሆይ እና ንጉሣዊ ቤተሰብ ጋር የኔዘርላንድስ ንጉሣዊ ቤተሰብን ባስተናገዱ ጊዜ።*



*Princess Sophia (center back row) with princess Adey Imru, Woizero Fisseha Ayalew, Prince Mikael Mokonnen & Princess Ruth Desta. Front row left to right; Princesses Aida, Seble Desta & Tenegnework Haile Selassie with friends in Geneva, Switzerland.*
ከጀርባ ልዕልት ሶፊያከ (መካከል) ከልዕልት አደይ እምሩ፥ ወ/ሮ ፍስሃ አያሌው፥ ልዑል ሚካኤል መኮንን። ከፊት ከግራ ወደ ቀኝ ልዕልት ሰብለ፥ ልዕልት አይዳ እና ልዕልት ተናኘዎርቅ ኃይለ ሥላሴ ከወዳጆቻቸው ጋር በጄኔቫ ስዊዘርላንድ።



*Princess Sophia with his Majesty and the Imperial Ethiopian family (c. 1960s)*
*ልዕልት ሶፊያ ከግርማዊ ጃንሆይ እና ንጉሣዊ ቤተሰብ ጋር።*



*Princess Sophia Desta sitting at the feet of His Majesty Emperor Haile Selassie and Empress Menen*
*ልዕልት ሶፊያ ደስታ ከግርማዊ ጃንሆይ እና ግርማዊት እቴጌ እግር ስር ተቀምጠው።*

*Dearest Mama,*

*You were one of a kind, sparkling imperial jewel hard to find, and hard to keep. You lived your life for others and left little for yourself. You were a royal princess but you chose to live a modest life. I didn't understand all of it but you and your creator knew better. You lived life the way it should be and you will always be the world's best example of what a person should be.*

*Rest in peace forever* 💔

*~Emebet Hannah Mariam Dereje*

የምወድሽ እማማ

ልዩ የማትተኪ የማትገኚ የማትያዢ እንቁ ነበርሽ። ሒወትሽን ለሌሎች ኖረሽ ለራስሽ ምንም አልተውሽም። ልዕልት ነበርሽ ግን በትሕትና ነው የኖርሽው። ለእኔም ሁሉም ባይገባኝም አንቺና ፈጣሪይሽ የተሻለ እውቀት አላችሁ። ሒወትሽን በትክክለኛው መንገድ ኖረሻታል እና ለሁል ግዜ የሰው ልክ ምሳሌ ሆነሻል።

በሰላም እረፊልኝ። 💔

~ እመቤት ሀና ማርያም ደረጀ።

